# ጋዜጠኛውም ነቢይ ሆነ፤ ሕዝባዊ አመጹም በየድረ ገጹ ደራ!

ከመላኩ ይስማው

አላዋቂ ሳሚ ይላሉ የሀገራችን ሰዎች። አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት ቅዱስ መጽሐፍ አጠበች የተባለውም ይሰራል። በአፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ እየነፈሰ ያለው የሕዝባዊ አመጽ ነፋስ ኢትዮጵያንም ይነካካታል በሚል ያለው ተስፋ ብዙዎችን ተድብቀው ከነብሩበት ዋሻ አውጥቷል። ለደግ የተነሱት ቁጥር በመጠኑ ሲሆን አብዛኛው ግን ለቦታና ታሪክ ሽሚያ፣ ነገር ዓለሙን ለማደበላለቅ ነው።

የፖለቲካ ጥራዝ ነጠቆች የፈሉባት ሀገር ኢትዮጵያ ከሆነች ውሎ አድሯል። ጡረታ ሲወጡም በፖለቲካ ሊዝናኑ የሞከሩ ሞልተዋል። እግረ መንገዳቸውንም ዝብርቅርቅ ፈጥረዋል። በተለይ በአሜሪካ ያሉና የከበሩ አንዳንድ ዜጎች — ዓባይም ቢሞላ ባይሞላ የራሱ ጉዳይ ነው በሚል ስሜት -- የተገነባውን ሲይንዱ፣ ሲበጠብጡና ሲያፈርሱ መቆየታቸው የተለመደ ነው። የድረ-ገጾችና ፓል ቶኮች ሚና ሁሌም ቀና አልነበረም፣ አይደለምም። ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉ በተባለው ዓይነት (ማቴዎስ ምዕራፍ 24)፣ በፖለቲካው መንደር ጸሐይ ጨረቃን በእጅ ይዘናል ማለት ከከጀሉት ውስጥ ጋዜጠኛው እስክንድር ነጋ አንዱ ነው። በእስክንድር ላይ ተገቢው ትችት ለመሰንዘር፣ "እነሆ የአብ ልጅ መጥቶልናል" በዝተዋልና፣ ጫሚታቸውና ጥርስ ማፋጨታቸው የሚበረክት የመሆኑ ፍራቻ ቢኖርም፣ የሕዝባዊ አመጹን በተመለከተ ግን ተነበየ ሲባል በዝምታ ማለፉ ሀገርን ስለሚጎዳ "ምነዋ ነብዝ አደብ ብንገዛ?! ተደናግረን ባናደናግር?!" ማለቱ ግደታ ይሆናል። ጋዜጠኛው በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ቆስቋሽነት ሕዝባዊ አመጽ ሊነሳ ይችላል ብሎ ማለቱ "ሰይ ብል ባንከረባብት" ዓይነት መላ ምት ከመሆን አልፎ ትንቢት አይሆንም። ተማሪዎች መሰለፍ ላይ ቀደም ይላሉና፣ ነገም ይህ ይከሰታል ማለት ይቻላል። ግን ትንቢቱ "ወይ ወንድ ወይ ሴት ትወልጃለሽ" ብጤ ትንቢት ነው። ታሪክን አለማውቅንም ያሳያል።

"ነቢዩ" እስክንድር እንዳለው ሳይሆን የቀድሞዎቹ ተማሪዎች በጋራ ሊነሱ የቻሉት በኮሙኒዝም ስላመኑ አልነበረም ፡፡ ያኔ "መሬት ለአራሹ" ዓይነት መሰረታዊና አስተባባሪ ጥያቄዎች ነበሩ ስለተባለውም ዛሬ በወያኔ ላይ ሊነሱ የሚችሉ መሰረታዊ የማታገያ ጥያቄዎች ከያኔ በበለጠ በሽበሽ ናቸው። ለምሳሌ፣

የጉሮ ውድነት ይቀንስ፣ የቫት ግብር ይነሳ፣
የሀገራችን መሬት ለባዕዳን መሸጡ ያብቃ፣ የአርሶ አደሩ መፈናቀል ያከትም
መሬት ለአራሹ
ስራ አጥነት ይወገድ፣
ለሱዳን የተሰጠው የሀገራችን መሬት ይመለስ፣
የብሄረሰብና የሀይማኖት ልዩነትና አድልኦ ያብቃ፣
በሀጻናት መነግዱ ያከትም ፤ እህቶቻችን ለዘመናዊ ባርነት አይዳረጉ
በሙስና የተጨማለቁ ባለስልጣናት ይወገዱ፤ለፍርድ ይቅረቡ፣
ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ፣ በፖለቲካ ድርጅቶች ላይ ያለው እገዳ ይነሳ
በሕዝብ ላይ ፍጅት የፈጸሙና ያስፈጸሙ ሁሉ ለፍርድ ይቅረቡ

እንጨምር? ብዙ ማለት ይቻላል።

ስለዚህም ወጣቱንም ሕዝብንም ለአመጽ የሚገፉ ብዙ ጥያቄዎች አሉ — የወያኔ አገዛዝ ይወገድ የሚለው ያውም ሳይነሳ ፡፡ ታዲያ ምነው ሕዝባችን ጫንቃውን ለመከራ ያመቻቸ መስሎ አላምጽ አለ? ለዚህ ሀቀኛው ምክንያቱ መፈለግ አለበት። የቀድሞ ተማሪዎች በኮምዩኒዝም ርዕዮት ተባብሩ የሚለውም መሰረተ ቢስ ነው። በጊዜው ግራ ክንፍ የነበሩ ( ክሮኮዳይል ወዘተ ስብስቦች) ብቅ ብቅ ቢሉና የእንቅስቃሴው አራማጆችም ቀስ በቀስ ወደ ግራነት ቢሳቡም፣ በመሰረቱ ተማሪዎች ኮምዩኒስቶች ብለው ሊጠሩ የሚችሉ አልነበሩም። ብዙሃኑም ስለዚህ ኮምዩኒዝም ስለተባልው ቃል ያላቸው ግንዛቤ ጠንካራ አልነበረም። ስለዚህም ያያዛቸው ዋነኛው ምክንያት ርዕዮት ሳይሆን በሀገሪቷ ለውጥ መምጣት አለበት የሚለው የጋራ ግንዛቤያቸውና በተለይም ለዚህ ለውጥ ሊታገሉ መቁረጣቸው ነው።

ተማሪዎች ያነቧቸውና የተሰለፉባቸው  ያቂዎች ሁሉ ኮምዩኒስትነትን አቀንቃኝ ሳይሆኑ በከብርቴ ዴሞክራሲ ጥያቄ ስር የተጠቃለሉ ነበሩ። ለምሳሌ

መሬት ለአራሹ፡
ድህነት ወንጀል አይደለም፡
ድሀው  ይማር
ባሕላችን አይርከስ
በእርሶ እድሩ ላይ የተጫነው ግብር ይሰረዝ
ሰላማዊ ሰልፍን የሚከለክለው የሕግ ረቂቅ ይሰረዝ
የሚሉትን የዚያን ጊዜ ጥያቄዎች መጥቀስ ይቻላል።
የነበረው ስርዓት ይውገድ በሚል ሰልፍ አልተደረገም። ኮምዩኒስት ስርዓት ይምጣልን ሰልፍም አልተደረገም። ከዚህ ሌላ በየካቲት 66ም ቢሆን የተማሪዎች ሰልፍ አብዮቱን አልለኮሰም። የታክሲ ነጂዎች አድማ፡ የነገሌ ቦረና ወታደሮች አድማ የአስተማሪዎች (ሴክቶሪያል ረቪው የተባለውን በመቃወም) አድማ ናችው ለኳሽ የነበሩት። "ነቢዩ" እንዳለው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ዛሬ አመጽን ለኳሽ ከሆኑ እሰየው ነው። ባለው ክፍፍልና የቁርጠኛነት መቅጠን ግን ይህ ለመሆኑ ጥርጥር ቢገባን አንወቀስም። ከታሪክ ግን ሀቅን መማር ተገቢ ነው፡ይጠቅማል።

ሁሉም አዋቂ ሁሉም ሰባኪ ሆኗልና፣ ከተመክሮም ከዛሬውም ለመማር የተነሳው ጥቂት ነው። የታሪክና የቦታ ሽሚያ እሽቅድምድም የተጀመረ ይመስላል። ስንቱ ነው የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ መሪም መስራችም ነበርኩ የሚለን? ስንቱ ነው በኢሕአፓ ቆይታው የሳምንታት ወይ አጭር ሆኖ ሳለ ስለዚህ ድርጅት ታሪክ ተራኪ ሆኖ የተገኘው? ቀደም ይባል እንደነበረው " አስመሳዩ  ተራማጅ ወይም ታጋይ" ፈልቷል። የህዝብ ጎራ ከነዚህ ባለመጽዳቱም ግራ መጋባት ሰፍኗል። ዛሬ በፖለቲካው መድረክ መሪ አስባሳቢ ሆነው የሚተረተሩልንን ስንመረምር፣ ለምን ለወያኔ የሚያመች ቅስቀሳ እንደሚደረግ መገንዘብ እንችላለን። ግንቦት 20 መስቀል አደባባይ ጠብቀን ማለቱ ለምን ይጠቅማል ለወያኔ ካልሆነ ? ለማደናገር ነው ከተባለም ወያኔ ይህን ያህል ጅል ቢሆን ለስልጣንም ባልበቃ ነበር። በቱኒዝያ ታይቷልና በኢትዮጵያም እናካሂዳለን ብለው የሚባዝኑት ደግሞ (ኮረንቲውም ኮምፒዩተሩም በሌሉበት ሀገር!) ምን ያህል ከሀገራችው ተጨባጭ ሁኔታ መራቃቸውን ያሳየናል።  በድረገጽ ደረጃ አብዮትን በራሳቸው ለራሳቸው አፈንድተው "እሲይፕ ባለማ" የሚሉት ለሀገር ምንም ጠቀሜታ የላቸውም፤ ከማደናገርና ለራሳቸው ርካሽ ዝናን ከመፈለግ ሌላ።  "እያደር በዛ፤ የእኔ ወንድነት፤ / እምና አይጥ ገደልኩ፤ ዘንድሮ ድመት።" እያለ እንደሚፎክረው ሰው ቢጤ።

ያበጠው ይፈንዳ፣ ሀቁም ይነገር ካልን፣ ለትግላችን ትልቁ ዕንቅፋት ሆኖ የቆየው የተቃዋሚ ድርጅቶች ይዞታ መሆኑ ግልጽ ነው። እነ ሰየና ገብሩ አስራትን፡ እነ በየን ጴጥሮስንና ልደቱን ወይ የሱን የታወቀ የወያኔ ሰላይ ምትኩን ይዞ ድልን መሻት ዘበት ነው። የኢትዮጵያ አብዮት በቴሌቪዥንም፡ በድረ-ገጽም በግንቦት 20 ም አይፈነዳም። የሕዝብ/ ጎራ ከአሁኑ ከአስመሳዮችና  ሰርጎ ገቦች መጽዳት አለበት። የኢትዮጵያ ሰርየት ከአስመራ ቤተ መንግስት መቸም አይወለድም። ኢትዮጵያዊነትን ነጋ ጠባ ከሚከዱ ጋር መተቃቀፍን የሚሰብኩ ሀገርን የሚጎዱ ሐሳዊ መሲሆች ናቸው።

ነቢይም መሪም ከማለታችን በፊት ዓይናችንን ከፈት አድርገን ማን ማን ነው ብለን መጠየቅ መመርመር ይገባናል።  መዳቡን ወርቅ፡ ቅራሪውን ፊልተር እንዳንል ወይም ጉፋያው የሰባ  ሙማ እንዳይመስለን። እንዳንታለል። ድል እንዳንነጠቅ። መቀለጃ እንዳንሆን። አብዮትና ሕዝባዊ አመጽ ጨዋታ አይደለም። ሕይወትን ይጠይቃል፡ የሀገርን የነገ ዕጣም ወሳኝ ነው። ስለዚህ በየድረገጹ የዝና ፈላጊዎች፡ ጥራዝ ነጠቆች፡ አልባሌ ነቢዮች፡ አደራ ምሁር በሉን ባዮችና ቀላጆች መጫወቻ መሆን የለበትም።  እንኳን የሀገርና የሕዝብ ዕጣ ፈንታን በሚወስን ጉዳይ፤ የግል ቤትም ሃላፊነት የሚሰጡት ሰው ታሪኩን ይጠየቅ የለ።